# አዬር በአዬር!

## ሳይማሩ ባለዲግሪ፣ሳይመረጡ ያገር መሪ!

ታህሳስ 23 ቀን 2013 ዓም(01-01-2020)

መቼም ካለፉት ሃምሳ ዓመታት ወዲህ በአገራችን መሬት ላይ ብቻ ሳይሆን በሃይቆቿም ላይ ያልነበረ አረም መብቀሉን እያዬን ነው።ምንጩ ያልታወቀ እንቦጭ የተባለ የወንዝ ላይ አረም የጣናን ሃይቅ ሽፍኖ በአሳውና በአሳ አጥማጁ ኑሮ ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።አረሙን ለማጥፋት የሚደረገው እርብርቦሽ ቢኖርም እስከ አሁን ድረስ አጥጋቢ ውጤት አላሳዬም። ትግሉ ግን ይቀጥላል።በሌላውም ዙሪያ ያገራችን ሰማይ በአንበጣ፣ምድሩ ደግሞ በጎሰኞች ተወሮ በችግር ላይ ችግር እዬተደራረበ አገር እንዳገር የመቀጠሏን ነገር ካሳሳቢ ደረጃ ላይ አድርሶታል። በሌላው በኩል አገርን ለመለወጥ በሚያስችለው  የእውቀት መስክ በሆነው የትምህርት ዘርፍ ላይ የሚታዬው ደባና ተንኮል አገራችንን ወደ ፊት ከማራመድ ይልቅ ባዕዳን  ለሚፈልጉት ዓላማ አስፈጻሚ የሚሆኑ በምሁር ስም ሹመት የሚሰጣቸው የሰው አረሞች የሚፈለፈሉበት ሆኗል።

በሌላው ዴሞክራሲያዊ  አገር እንደሚታዬው የአገሪቱን የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ዘመኑ  የሚጠይቀውን የፖለቲካ ዕውቀት፣ የትምህርት ደረጃና ብቃት አሟልቶ መገኘት የግድ ይላል። በአገራችን ግን በተግባር የሚታዬው ከዚያ ለዬት ይላል።በጉልበት ስልጣን መያዝና  ከያዙ በኋላ  የትምህርት ማስረጃ  አዬር በአዬር በሆነ የጥቅም ልውውጦሽ በተጭበረበረ መልኩ ይዞ መገኘት አንዱ ስልት ከሆነ ውሎ አድሯል ማለት ብቻ ሳይሆን አብሮ አርጅቷል ማለቱ ይቀላል።

በደርግ ዘመን ለትምህርት ወደ ሩስያና ሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ከሚላኩት ተማሪዎች ጥቂት የማይባሉት የሚላኩበት መመዘኛው ያላቸው የትምህርት ደረጃና ብቃታቸው ታይቶ ሳይሆን ለወታደራዊው አምባገነን መንግሥት ካላቸው ታማኝነትና ከጁንታ አባላቱ ጋር ካላቸው የጥቅም ወይም የዝምድና ግንኙነት አንጻር የሚሰጥ ዕድል እንደነበር በመንገዱ ያለፉት ሳይቀሩ የሚክዱት አይደለም፤ቢክዱትም ተምረው ባለዲግሪ ተብለው ከተመለሱ በኋላ የሰጡት ጥቅምና አስተዋጽኦ ዋና ማስረጃ ነው። እነዚህ ሰዎች በዲግሪ ደረጃ ለምረቃ የሚያበቃቸውን ትምህርት በሚገባ ተከታትለው ከጨረሱት መካከል የተዘሩ አረሞች ነበሩ።ጊዜያቸውን ያሳለፉት ኮረዳ በማሳደድና የንግድ ሸቀጥ እዬሰበሰቡ በአገር ቤት ንብረት ለመያዝ በመሯሯጥ ላይ ነበር።በየጊዜው ወደ ምዕራቡ አገር በተለይም ወደ ምዕራብ ጀርመን በመመላለስ ሸቀጣ ሸቀጥ እዬሰበሰቡ ወደ አገርቤት ከመላካቸው ጎን ለጎን የትምህርት ቤቱን መምህራን በማያገኙት የምዕራቡ አገር መጠጥና የጅንስ ሱሪ እዬደለሉ ላልተማሩበት ትምህርት የዲግሪ ባለቤት ለመሆን በቅተዋል። በዚህ መልኩ የተማሩት ነበሩ እንግዲህ አገር ቤት ተመልሰው የልዩ ልዩ ተቋማት መሪዎችና ሃላፊዎች ወይም ካድሬዎች የሆኑት።በጤና ዘርፉማ ያደረሱት ጥፋት አያድርስ ከማለት በቀር ተዘርዝሮ አያልቅም።እንደው ሆድ ይፍጀው ብሎ ማለፉ ይቀላል። ደግሞስ ከስምንተኛ ክፍል በላይ መደበኛ ትምህርት በሌለው መንግሥቱ ሃይለማርያም ከሚመራው መንግሥት የትኛው የትምህርት ጥራት ይጠበቃል? ለስርዓቱ አገልጋይ የሆነ ሁሉ የሚሾም የሚሸለምበት ወቅት እንደነበር ማንም አይክደውም።የተማሩትንማ በግፍ ጨፍጭፎ ወይም አሰድዶ አገራችንን የምሁር ደሃ አድርጓት የለም እንዴ?። ይኸው ጉደኛ አይደለም እንዴ አገራችን  ብቻ ሳትሆን ለሌሎች የአፍሪካ አገሮች መመኪያ የነበረውን  የሓረር ጦር አካዳሚ ዘግቶ ብዙ ምሩቃን መኮንኖችን ያሳደደና የገደለው?ከዚያም ቀጥሎ አገራችን በተገንጣይና አስገንጣይ ሃይሎች በተወረረችበት ጊዜ፣የጦር ሃይሉ የሞት የሽረት ፍልሚያ በሚያደርግበት ጊዜ መሪዎችን ገሎ፣ ከውጭ ሃይሎች ጋር ተመሳጥሮ ጦሩን በትኖ የፈረጠጠውና በኢትዮጵያ የመሪዎች ታሪክ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ጥቁር ነጥብ የጣለው?ሰሞኑን ደግሞ በእሱ አሸቃባጮች እንደ አገር ወዳድ ተቆጥሮ ከስደት ይመለስ የሚለው ጫጫታ መደመጥ ተጀምሯል።አድናቂዎቹ በቀይ ሽብር እጃቸው በደም የጨቀዬ ወይም የነሱ ልጆች ቢሆኑ እንጂ ትክክለኛውን ታሪክ ከሚረዳ ኢትዮጵያዊ በኩል የሚጠበቅ አይደለም። ይህ ከፍትሕ አምልጦ የኖረ ወንጀለኛ ቢመለስ ካቴና እንጂ የአበባ ጉንጉን ሊጠብቀው አይገባም።ቅጣቱንም የሚያገኘው በጦር ፍርድ ቤት እንጂ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊሆን አይገባውም። በአገር ላይ ክህደትና ወንጀል የፈጸመ በሕግ አለመጠዬቅ ባህል ሆኖ እንዳይቀር ማሳያ ተደርጎ መወሰድ አለበት።ማረጋገጫውም በዚህ ወንጀለኛ ላይ የሚኖረው አቋምና የሚተላለፈው ፍርድ ነው።

ወደ አዬር ባዬሩ ዲግሪ ስንመለስ፣ላለፉት ሰላሳ ዓመታት በሰፈነውም ወያኔ መራሹ የኢህአዴግ ዘመንም እንዲሁ መሪዎቹ ሳይቀሩ ለከፍተኛ ትምህርት የበቁና የእውቀት ባለጸጎች ሳይሆኑ በአገር ጥላቻ የተካኑ ነበሩ። መመሪያቸውም ከአንድ

ብቃት ካለው ምሁር ተቃዋሚ ይልቅ አንድ መሃይም የድርጅት አገልጋይ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የወያኔ መሪ የነበረው ሟቹ መለስ ዜናዊ ሳይቀር በአደባባይ ገልጾታል። የኋላኋላም የነበረውን የማህይሞች አመራር ውጭያዊ ገጹን ለመቀዬር ቱቦ ቱቦ መሪዎቹ የርቀት ትምህርት በሚል ሽፋን በአዬር ባዬር የተለያዩ ድግሪዎች ባለቤቶች እንዲሆኑ የማድረግ ጥረት ተደርጓል።እንደሚወራው ከሆነማ አብዛኛዎቹ ባለዲግሪ የሆኑት ገንዘብ ከፍለው ባሰሩት የምረቃ ጽሁፍ ነው ይባላል።አይሆንም አይባልም፤በገንዘብ ብዙ ነገር ይገኛል። በደጋፊ የአውሮፓ አገራት ከሚገኙ እውቅ ዩኒቨርሲቲዎች አንድም ቀን በዩኒቨርሲቲው ግቢ ሳይውሉ ቢኤ፣ማስተርስና ዶክትሬት ዲግሪ የተቻራቸው ብዙዎች ናቸው።በአካልም ትምህርት የተከታተሉት ቢሆኑ በተግባር ላይ ውለው የሚሰጡት ጥቅምና የሚያሳዩት ምግባር ለተሰጣቸው የትምህርት እውቅና ወይም ዲግሪ የሚመጥን አልሆነም። በውጭ አገር ተማሩ ብሎ ከማለት ቆይተው ገቡ ማለቱ ይቀላል። ትምህርት ከኋላ ቀርነት አስተሳሰብ የሚያወጣ፣ሕዝብን ከጥፋትና አገርን ከውድመት የሚያድን፣ ለተሻለ ደረጃና ስርዓት የሚያበቃ፣ የከፍተኛ ስነምግባርና ስብእና የበጎ አመለካከትን ጸጋ የሚያላብስ የተሃድሶ ቡራኬ ወይም ከድንቁርና ጨለማ ወደ ብሩህ ህሊና የሚገቡበት ቁልፍ ነው።የተማረ ሰው ሌላው ቢቀር ጎሰኝነትን ይታገላል እንጂ ወርዶ ወርዶ እራሱ ጎሰኛ አይሆንም።

አስመሳይ ምሁራን ከሚፈልቁባቸው አገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት የተሰለፈችው አንዷ አገር ኔዘርላንድ ነች።በኔዘርላንድ ውስጥ የታወቁ ዩኒቨርሲቲዎች ሲኖሩ በተጨማሪም የውጭ አገር ዜጎች በተለይም በሥልጣን ዙሪያ ያሉ እንደ ችግኝ በዲግሪ የሚፈለፈሉበት የማህበራዊ(ሶሻል) ጥናት የሄጉ ዓለም አቀፍ ኢንስቲቱይት ዋናውን ቦታ ይይዛል።በዚህ ተቋም ብዙ ኢትዮጵያውያን ያለፉበት ሲሆን የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት አዬር ባዬር በተደረገ የእጅ አዙር ግንኙነት የዲግሪ ባለቤቶች ሆነውበታል።በአካል በመሳተፍም መረራ ጉዲና፣አረጋዊ በርሄና የመሳሰሉት ይገኙበታል። አሁንም የዶክትሬት ባለቤት መሆኑ የሚወራው ለማ መገርሳ በአዬር ባዬር ትምህርት ተመረቀ የሚባለው በዚቹ ጉደኛ አገር በኔዘርላንድ ውስጥ ነው።አንድም ቀን በአካል ክፍል ውስጥ ገብቶ መማሩ ሳይታወቅ፣ከመምህራኑ ጋር የአካል ግንኙነትና እውቅና ሳይኖረው የዶክትሬት ዲግሪ ባለቤት መሆኑ ሲነገር የሚያጠያይቅ ነው።በተለይም አሁን የዶክትሬት ዲግሪ አገኘበት የሚባለው ቦታ በቅጡ ያልታወቀ መሆኑ ጥርጣሬውን ያሳድገዋል።አንድ ጊዜ ላይደን፣ሌላ ጊዜ ሄግ አሁን ደግሞ አምስተርዳም እዬተባለ በመነገር ላይ ነው።እንግዲህ እነዚህን የመሳሰሉት ዶክተር ተብዬዎች ናቸው በዬጎሳው ድርጅት ውስጥ ገብተው የመሪነቱን ቦታ የያዙትና አገር የሚያምሱት።ከጎሰኝነት የበለጠ ምን ድንቁርና ይኖራል?

በዚችው አገር ውስጥ እዬኖሩ እንደማንኛውም ያገሪቱ ዜጋ ተምረው ጥሩ ውጤት ያመጡ ኢትዮጵያውያኖች እንዳሉም መዘንጋት የለበትም። ትንሽ የማይባሉት ኢትዮጵያውያን የህክምና ባለሙያዎች፣የእርሻና የግንባታ መሃንዲሶች ይገኙበታል።እዚሁ ከኢትዮጵያውያን ወላጆች ወይም ፤ከሌላ ዜጎች የተወለዱት ቅይጥ ኢትዮጵያውያኖችም ለከፍተኛ ትምህርት በቅተው፣በጥሩ ውጤት ተመርቀው ሥራ የያዙና አሁንም በትምህርት ላይ ያሉ መኖራቸው የሚዘነጋ አይደለም።

እነዚህ ባለፉበት መንገድ ያላለፉትን ለፖለቲካና ለኤኮኖሚ ጥቅም ሲባል በሥልጣን ላይ ያሉትን የዲግሪ ባለቤት ማድረግ ግን በአገር ላይ ብቻ ሳይሆን በእውቀት ላይ የሚደረግ የጥፋት ዘመቻ ነው።ከዚያም አልፎ ተርፎ የትምህርት ተቋማቱን ለእጅ አዙር ቅኝ መንደርደሪያ መሣሪያ የሚሆኑትን የሚያዘጋጁበት ፋብሪካ የማድረግ ያህል ነው።ድርጊቱ በዲግሪ ሽፋን ችሎታ የሌላቸው ሰዎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ሲሆን ድርጊቱን በምሳሌ ብንመለከተው ባዶ ቅልን በሚያምር የገና ስጦታ መጠቅለያ ወረቀት አሳምሮ ማቅረብ ወይም ያልተጠረበ ድንጋይ በሚያምር የመገልበጫ መኪና ጭኖ መዘርገፍ ይመስላል።ጉዱ የሚፈላው ገላልጠው ሲያዩት ነው።

የኔዘርላንድ ጉድ በዚህ ብቻ አያበቃም፣ከአርባ ዓመት በፊት ለተገንጣይ ሃይሎች ታደርግ የነበረውን እርዳታ ለጊዜው ትተን ከሦሥት ዓመት በፊት ማለትም የአሁኖቹ አገር መሪዎች የኦህዴድ/ብልጽግና አባላት ሥልጣን ላይ ከመውጣታቸው በፊት ቅድመ ስልጠና የተሰጣቸው በዚህቹ በኔዘርላንድ ውስጥ ነበር።በሌሎቹም የአውሮፓ አገሮች በተለይም በቤልጅዬም፣ጀርመን፣እንግሊዝና ስካንዲኔቪያ አገሮች እንዲሁ ተመሳሳይ ድርጊት እንደተፈጸመ ከመንግሥት ጋር ካላቸው ቅርበት መረዳት ይቻላል።አሁንም ላለው ጎሰኛ መንግሥት ጠበቃና ተከራካሪዎቹ እነዚሁ አገራት ናቸው።የዘረጉት የኤኮኖሚ እንቅስቃሴና የወደፊት አፍሪካን በእጅ አዙር የመቆጣጠር ዓላማ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አላደረጋቸውም። ጥቅማቸው እስከተጠበቀ ድረስ ኢትዮጵያ ብትፈራርስ ደንታ አይኖራቸውም።በዚህ ደባ ውስጥ የሚዳከሩት መንግሥታቱ እንጂ ሕዝቡ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት።ሕዝብ ለሕዝብማ ያለው ግንኙነት በመከራ ጊዜ መረዳዳት ነው።በድርቅ ወቅት፣በሰብአዊ መብት፣በስደተኞች ጥያቄ፣ድምጻቸውን ከማሰማት ቦዝነው አያውቁም። ከውጭ አገር ተወላጆች ጋር በቤተሰብነትና በጉርብትና በሰላም አብሮ መኖሩ የሕዝቡ መገለጫዎች ናቸው።የዬአገራቱ ሕዝብ

የጥፋቱ አካል አይደለም።በመንግሥት ሚድያ ግን የሚረጨው ወሬ የውዥንብር ሰለባ ሊያደርገው ይችላል።ያንን ለመከላከል ኢትዮጵያውያን በያሉበት ስለ ሃገራቸውና የሚኖሩበት አገር መንግሥት ስለሚፈጽመው እኩይ ተግባራት ለሕዝቡ በቂ መረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያ አገራችን እኮ እንዳሁኑ ዘመናዊ ትምህርት ሳይስፋፋ፣ዲፕሎምና ዲግሪ የተባሉት መመዘኛዎች ሳይኖሩ በነበራት አገር በቀል መንፈሳዊ ትምህርት የተካኑ፣ስነምግባር ያልጎደላቸው ዜጎች በነጻነት የመሯትና ያስከበሯት አገር ነች።አሁን ከእውቀትና ሃብት ማማ ላይ የደረሱት አገራት ሳይፈጠሩ መንግሥታዊ ስርዓት የዘረጋች አገር ናት። የምሰነዝረው ሃሳብ የትምህርትን ጥቅም ለማቃለል ሳይሆን በትምህርት ጀርባ የሚጎነጎነውን ሴራ ለማጋለጥ ሲሆን በትምህርት ስም የሚግበሰበሰውን የዲግሪ ተሸካሚና የባእዳን ወኪል በቅጡ የሚመዝንና የሚፈትሽ አገር በቀል ተቋም መኖር እንደሚኖርበትም ለማሳሰብ ነው። በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ለትላልቅ ዩኒቬርስቲዎች መምህር የሆኑ ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች በኢትዮጵያና በውጭ አገራት የሚኖሩ ለአገራቸው የሚያስቡ ኢትዮጵያውያን ስላሉ የአገራችንን የትምህርት ደረጃና በውጭ አገር የተመራቂዎቹን ችሎታ በቀላሉ ሊፈትሹ የሚችሉበት ተቋም ሊኖር ይገባል።ከነዚህ ዜጎች በላይ የአገራችንን የትምህርት ጥራትና የተመራቂውን ችሎታ የሚያረጋግጥና የሚያስከብር አይኖርም።ዲግሪ የሌቦች ባለሥልጣናትና የወራሪዎች የሸርክና ውል ማረጋገጫ ወይም የፈቃድ ወረቀት እንዳይሆን መከላከል ይገባል ባይ ነኝ።

በትምሕርት መስኩ እንደሚታዬው ማጭበርበር በፖለቲካውም የሚታዬው ማጭበርበር እንዲሁ ቅጥ ያጣ ነው።ምርጫ ሳይደረግ በዚህም በዚያም ብሎ፣ወይም በኩዴታ ሥልጣን ላይ የወጣን አምባገነን እውቅና መስጠቱ የተለመደ ነው።ለዚያም ነው “ሳይማሩ ባለዲግሪ፣ሳይመረጡ የአገር መሪ” ለማለት ያደፋፈረኝ።አገራችን ሕዝብ ባልመረጣቸው አምባ ገነኖች መዳፍ ስር ለረጂም ዓመታት ስትዳሽቅ መኖሯ አይካድም።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለይምሰል ምርጫ ቢካሄድም ሥልጣን ላይ የሚወጣው ድምጽ ያጭበረበረና የውጭ አገራት የሚረዱት የጎሰኞች ቡድን ነው።ለዚያም መሳሪያ የሚሆን እንደምርጫ ቦርድ አይነቶቹን በጥቅም ሰንሰለት አስሮ የምርጫ ውጤቱን ወደሚሹት አቅጣጫ ይመሩታል። አሁን የምርጫ ቦርድ ተብዬው መንግሥታዊ ተቋም የሚንቀሳቀስበት ባጀት የሚገኘው በአብዛኛው ከኔዘርላንድና ጀርመን እንዲሁም ከአውሮፓ ህብረት በኩል ነው።ገንዘብ የሰጠ ደግሞ የመወሰን መብቱ ከፍተኛ ነው።ምርጫ ቦርድ ሣር እያበሉ የሚጋልቡት ፈረስ እንደማለት ነው።ለመንግሥት አደጋ የሚሆኑትን እውነተኛ አገር ወዳድ ተቀናቃኞችን ከማይረቡት ጋር ቀላቅሎ ለማሶገድ የሚጠቀሙበት መሳሪያ ሆኗል።

እነዚሁ ለዲሞክራሲ ቆመናል የሚሉ መንግሥታት በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የሰብአዊ መብት ሲጥስ፣ፍትሕ ሲደፈጥጥ፣የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ ሲሳነው፣የጎሰኞች አሸባሪ ቡድን በመንግሥት ድጋፍ ያሻውን ሲያደርግ፣የሰው ልጅ እንደ ጎመን ሲበላ፣ሲገድል፣ሲፈናቅል፣እያወቁና ድምጻቸውን እንዲያሰሙ ተደጋግሞ ቢጠዬቁም ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዋል።ዱሮውንስ ያልተማረ ሰው ተምሯል ይምራችሁ ብለው ለሚልኩ መንግሥታት ለሚፈጸመው እኩይ ተግባር ምን ደንታ ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል? ዶክተር፣ፕሮፌሶር ከፍ ሲልም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰላም አባት እያሉ መሸለምና ማሞከሸ ከዓላማቸው አንጻር የሚጠበቅ ስለሆነ የሚገርም አይሆንም።ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት!

በሥልጣን ላይ ያለው የኦሮሞ ጎሳ ቡድንና አጃቢዎቹ ዓላማቸው ኢትዮጵያን አጥፍቶ ወይም በታትኖ ኦሮሚያ የሚባል በታሪክ ያልነበረ አገር መመስረት መሆኑ በግልጽና በተደጋጋሚ ተነግሯል።ለኦሮሚያ የኤኮኖሚ ግብአት የሚሆን የሥልጣን ሽፋን የተሰጠው ዘረፋና የተቋም ግንባታ በሌላው ወገን ኪሳራ በመስፋፋት ላይ ነው።ኦሮሞ ያልሆነው የከተማ ኑዋሪ ለዘመናት የኖረበትን ቦታ በስበብ ባስባቡ እዬተቀማ፣የማይችለውን ህንጻ እንዲሰራ በማስገደድ ያልቻለውን በመንጠቅ ቤት አልባ ሆኗል።ሌላውም ከሃያ ዓመት በፊት በሊዝ ለብዙ ዓመታት የያዘውን ቦታ የሊዙ ጊዜ ሳያልቅ በኦህዴድ መራሹ አስተዳደር በአሁኑ የከተማ ቦታ ዋጋ ስሌት እንዲከፍል ተበይኖበት ችግር ላይ የወደቀው ከቁጥር በላይ ነው።በነዚህ ኪሳራ ለቱሪስት ገቢ የሆቴልና የመዝናኛ ቦታዎች ግንባታም እንዲሁ በስፋት ቀጥሏል።በጣም የሚገርመው ሕዝብ በትንሽ የአለላ(ሰንበሌጥ) ሞሰብ ላይ መብላት እያቃተው ለቱሪስት እይታ የሚሆን አርባ ቢሊዮን ብር የሚፈጅ የድንጋይ ሞሰብ ለመስራት ሽር ጉድ እዬተባለ ነው።ይህም የሚሆነው የኦሮሚያ ከተማ ነች በሚሏት አዲስ አበባ ውስጥ ነው።ለአገር የሚያስብ መንግሥትማ ቢኖር ኖሮ ይህንን አርባ ቢሊዮን ብር በተለያዩ የገጠር ቦታዎች በተለይም በእርሻው ዘርፍ ላይ ወይም የክፍላተ ሃገር ከተማዎች ለልማት ተቋማት ግንባታ ያውለው ነበር። በአንድ ቢሊዮን ብር ተመን አርባ ትላልቅ የሥራ ዘርፎች ያሉት የልማት ተቋም መዘርጋት በተቻለና በቀላሉ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሰው የሥራ ዕድል ባገኝ ነበር።ያ ግን የሚያስጨንቀው መንግሥት አይደለም።ጭንቀቱ ኦሮሚያ የተባለ አገር ለመፍጠር የሚያስችል ዝግጅትና ገንዘብ የሚሰበስብበትን መንገድ ማሰላሰል ነው።ብዙሃኑ የአምስት ብር ዳቦ ገዝቶ መብላት በማይችልበት አገር ውስጥ ጥቂቶቹ ለአንድ ገበታ እራት ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ አውጥተው የሚዝናኑበት አገር ቢኖር ኢትዮጵያ ብቻ

ነች። የሚዝናኑትም የአገሪቱን መሬትና የማዕድን ሃብቶች የሚቸበችቡት ባለሥልጣኖችና ተባባሪ ዘራፊዎች ናቸው።ሕዝቡማ እንደፈረደበት የበይ ተመልካች ነው። ያም ብቻ አይደለም በአገሪቱ በቂ የሕዝብ መጓጓዣ ሳይኖር ባለሥልጣናቱ ብዙ ሚሊዮን ብር  የሚያወጣ ውብ መኪና ሲያሽከረክሩ  ማዬት የእብደቱ ጣራ ከምን ላይ እንደደረሰ ማሳያ ነው። በአንድ አገር ውስጥ ሁለት የተለያዩ ዓለማት፣የብዙ ድሆችና የጥቂት መረን የለቀቁ ባለጸጎች አገር! ኢትዮጵያ!

አሁን ሱዳን ጋር የተገባው ግብግብ የስርዓቱ ውጤት ነው። አገር ወዳድ የሆነ ስርዓት በሌለበት አገር የሚገጥም ፈተና ነው።ይህ ለኢትዮጵያ ደንታ የሌለው ስርዓት ይዋል ይደር እንጂ ባዕዳን የሚጠይቁትን ከመፈጸም አይመለስም።በሰሜኑ የኢትዮጵያ ድንበርና በነዋሪው ሕዝብ ኪሳራ የራሱን የወደፊት ጥቅም ለማስከበር ሲል ያልሆነ ስምምነት ይፈጽማል የሚለው ስጋት ከግምት  በላይ ነው።

አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ያላቸው አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ያም በራስ የመተማመንና በዚያም ላይ መሰረት ያደረገ ችሎታቸውንና እውቀታቸውን አስተባብረው ሙብትና አገራቸውን ለማስከበር የሚችሉበት ሃይል መፍጠር ነው።ሃይል ካለ መሰማት አለ!ሃይል ካለ መከበር አለ!ሃይል የመሣሪያ ብቻ ሳይሆን የእውቀትም ጭምር ነው። ያም ቢሆን በተበታተነ መልኩም ቢሆን የማይናቅ ሃይል አለ።የሚጎለው ቢኖር መተባበር ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ በእውነተኛ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

አገሬ አዲስ